**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት**
**የድጋፍ ኮሚቴ በዩናይትድ ኪንግደም**
**United Ethiopian Democratic Forces**
**Support Committee in the UK**

## *<u>በተናጠል የሚደረግ ትግል ለተወሳሰበዉ የኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ አይሰጥም</u>*

የኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነትና አንድነት ከዳር እስከዳር ድረስ ያለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጋራ በከፈለው መስዋእትነት ተጠብቆ የቆየ እንጅ በተበታተነ መልክ በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ብረታት ወይም ደግሞ በአንዳች አይነት ምትሃታዊ ታአምር የቆየ አይደለም። ከታሪክም ሆነ ከልምድ እንደምንረዳዉ ለነጻነት ከተከፈለው ዋጋ በስተጀረባ ደግሞ በኢትዮጵያ ስም እየማሉና እየተገዘቱ ሃገራችንን ለጥቃትና ለችግር ያጋለጡና እያጋለጡ ያሉ ብዙዎች ናቸዉ። የአሁኖቹ ገዥዎቻችንም የዚህ የሁለተኛው ጉድ ወገን የዘመናችን ክስተቶች ናቸው። ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ለመጥራት አፋቸውን የሚከብዳቸው፤ ከፍቅር ይልቅ ቅራኔን፣ ከአንድነት ይልቅ መበታተንን የሚሰብኩ፣ በመንደር ደረጃ እያሰቡ ሀገርን የሚገዙ የዘመናችን ጉዶች ናቸው። በፖለቲካው፣ በምጣኔ ሀብቱም ሆነ በማህበራዊ ህይወት ዘረፍ የሀገራችንንና የህዝባችንን ህልውና የሚፈታተን የተናጠል ደርጅታዊ ፕሮግራማቸውን ነው የአገዛዝ መርሃቸው ያደረጉት።

የሃገራችን አብዛኛው ወገን ሠርቶ ለማፍራት፣ እራሱንናና ወገኑን ለመርዳት ከዛም አልፎ ሃገሩን ለመጥቀምና ከፍወዳለ የእድገት ደረጃ ለማድረስ የሚጥር፣ ሆኖም ግን ለፍቶ ደክሞ እንኳን ለሃገሩና ለራሱም የእለት ተእለት ኑሮ መሸፈን ያቃተዉ መሆኑን ስንረዳ እጅግ እያዘንን ነዉ። በኢትዮጵያችን እንደዚህ ያለዉ ክስተት ያብዛኛዉ ወገን እጣ ፋንታ እንደሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀዉ ግልጽ እዉነት ነዉ። ይህ እዉነት በአሁኑ ወቅት በግልጽና በጉልህ እየታየ የመጣ ለመሆኑ ብዙ ማረጋገጫ የሚያስፈልገው አይመስለንም።

ወጣት ኢትዮጵያዊ ሁሉ በተቻለ መጠንና ፍጥነት ከዉድ ሃገሩ ዉጭ ወጥቶ ለመኖር ያለ የሌለዉን ተበድሮም ተለቅቶም የሚከፍልበት፣ የተማረዉም ወገን እንዲሁ የሸመታትን ትንሽም ሆነች ትልቅ እውቀት ይዞ ወደ ተመቸው ሃገር መዉጣት ምኞቱ ከሆነ ሰንብቶአል። ነጋዴዉም፣ ገበሬዉም፣ ሰራተኛዉም፣ ስራአጡም በሙሉ ከችግር ለማምለጥ፣ አገር ለቆ ለመዉጣት መውጫ መንገድ የሚፈልግበት ጊዜ ሆናል።

ችግሩ የተፈጠረዉ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገራት ተለይታ መአት እንዲደርስባት የተፈረደባት ሃገር ሆና ሳይሆን በአስተዳደር ብልሹነት ምክንያት እንደሆነ የሚታወቅ ነዉ። በሃገራችን የተፈጠረዉ ችግር መፍትሄ ሊያገኝ የሚችለዉም ችግር ፈጣሪ የሆነዉን ብልሹ አስተዳደር በህብረት ሆኖ በመታገል ማስወገድ ሲቻል ብቻ ነዉ። በተናጠል የሚደረግ ትግል ምንም አይነት የትግል ታክቲክ መለዋወጥ ቢደረግበት ለተወሳሰበዉ የኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ ይሰጣል ብለን አናምንም። የግንቦት 1997 ምርጫ ሂደት ያስተማረንም ይኸንኑ የጋራ ጉዞን አስፈላጊነትና ወሳኝነትን ነዉ። በእንደዚህ ያለ የዉጥረት ወቅት ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጋራና በህብረት ባንድ ላይ በመቆም ሃገርን ለመታደግ የሚጥርበት ጊዜ እንጅ፣ ይኸ እንዲህ ነዉ ያኛዉ ደግሞ እንደዚያ ነዉ እየተባባለ እርስ በእርሱ የሚወነጃጀልበት ወቅት አይደለም። ዓላማችን ፍትህ፣ ዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት የተከበረባት ኢትዮጵያን ማየት እስከሆነ ድረስ ሀገርን ለማዳን፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማምጣት የተነሱ መላው የተቃዋሚ ሃይሎች ለዚህ አላማ በጋራ የማይቆሙበት መክንያት ይኖራል ብለን አናምንም።

ስለሆነም የኢዴኃሳ ድጋፍ ኮሚቴ በዩናይትድ ኪንግዶም፦

- ❖ በፖለቲካ አመለካከታቸዉ ምክንያት ብቻ የአቶ መለስ ድርጅት ወደስልጣን ኮርቻ በተቃረበበት ወቅት፣ ስልጣን ላይ በወጣበት ሰሞንና እስካሁንም ድረስ የታሰሩ የህሊና እስረኞች [የድርጅት መሪዎች፣ አባላቶችና ደጋፊዎች እንዲሁም ጋዜጠኞችና ሌሎች ሞያተኞች] በሙሉ ያለምንም ቅድመሁኔታ ከእስር እንዲለቀቁ።
- ❖ በዚሁ ዘረኛ አምባገነን ድርጅትና በተለጣፊ ካድሬዎቹ የግፍ አስተዳደር ህይወታቸው የጠፋ፣ ደማቸው የፈሰሰና እንግልት የደረሰባቸው ወገኖቻችን ፍትህ ያገኙ ዘንድ በነጻና ገለልተኛ አጣሪ አካል ተጣርቶ ከቁንጮ ቆንጮዎቹ ጀምሮ ወንጀል ፈጻሚዎቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ እየጠየቅን

ሃገራችን ኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርአት የሰፈነባት፣ የህግ የበላይነትና የሰብአዊ መብቶች የተከበሩባትና የሚከበሩባት፣ ዜጎች በመላዉ ሃገራቸው ተዘዋውረዉ በመስራት የስራቸዉን ፍሬ ባግባቡ የሚያገኙበት ትሆን ዘንድ፦

1. ኢትዮጵያዊያን የተቃዉሞ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክና የሙያ ማህበራት፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች እንዲሁም ሃቀኛ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ በአንድነት በመሆን ለዚህ ስርአት ህያው መሆን ጥርጊያዉን መንገድ በጋራ ማስተካከልና ማዘጋጀት ይገባናል ብሎ ያምናል።
2. ለዚህ ጉዞ የተቀነባበረና የጋራ አመራር ያለዉ አካሄድ እንደሚያስፈልግ ምንም ጥርጥር የለዉም። ቅንብር የሌለዉ አካሄድ ትግሉን ለማሰናከል ለሚፈልጉ ሰርጎ ገቦች መንገድ ስለሚከፍትና ህዝብንም ስለሚከፋፍል እንዲሁም ደግሞ ስልጣንን ከህዝብ ዘንድ በብልጣብልጥነት ለመስረቅ፣ አለዚያም ሀገርን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል እሳት እዚያም እዚያም ለመለኮስ ለሚቅበዘበዙ ጸረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ወይም ግለሰቦች በር ስለሚከፍት፣ የህብርት ትግል ጥያቄ ወሳኝ ነዉ።
3. የተከፋፈለና ያልተቀነባበረ አሰራር ዝንባሌዉ ወንጀልን የፈጸሙና በመፈጸም ላይ ላሉ የኢህአዴግ አመራሮችና ባለስልጣናት ተጠያቂነት ሽፋን መስጠት ነዉ።

ስለዚህ የኢዴኃሳ ድጋፍ ኮሚቴ በዩናይትድ ኪንግዶም የኅብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት የቀውጢ ጊዜ የጋራ ግብረ-ኃይል የመመስረትን እና የጋራ ጉባኤ የመጥራትን አስፈላጊነት ስለሚያምንበት እየአንዳንዱ ለሀገሩና ለወገኑ በጎ የሚያስብ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለዚሁ ግብ መሳካት የሚቻለዉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት እንጠይቃለን። የተቃዋሚው ወገን ሃይሎች ወደጋራ ትግሉ ጎራ ይቀላቀሉ ዘንድ ሁሉም በሚቻለው መንገድ ግፊት፣ ጥረት እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!*
*ድል የህዝብ ነዉ !!*

የኢዴኃሳ ድጋፍ ኮሚቴ በዩናይትድ ኪንግዶም፣ ግንቦት 1998

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.